# ስለምዘናዎች ወይም ፈተናዎች የወላጆች መመሪያ

*ለ2018-19 የትምህርት ዘመን*

## SAT (የትምህርታዊ ዝንባሌ /ስኮላስቲክ አፕቲቲዩድ/ ፈተና)

ምዘናዎች ወይም ፈተናዎች ለተማሪዎች፣ ለወላጆች እና ለትምህርት ባለሙያዎች (አስተማሪዎች) ተማሪዎች የየክፍል ደረጃቸውን እውቀት (ይዘት) ስለማወቅ አለማወቃቸው እና ለ21ኛው መ/ክ/ዘ ዝግጁ ሆነው ለመመረቅ ስለመቻል አለመቻላቸው ጠቃሚ መረጃ ይሰጣሉ። የምዘና ውጤቶቹ የልጅዎ ትምህርታዊ ዕድገት/ለውጥ በጥቅሉ ከሚያሳዩት ምዘናዎች አንድ መለኪያ እንዲሆኑ የታሰቡ ናቸው።

## ይህ ምዘና/ፈተና ምንድን ነው?

SAT ወይም የትምህርታዊ ዝንባሌ በሁሉም የኮሎራዶ አሥራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች የሚወሰድ ወሳኝ የሆነ የስቴት አጠቃላይ ፈተና ነው። በኮሌጅ ቦርድ የሚዘጋጀው የSAT ፈተና የየተማሪን እስከ 11ኛ ክፍል ድረስ ያለውን ትምህርታዊ ዕድገት/ለውጥ እና ለኮሌጅና ለሥራ ያለውን/ያላት የዝግጁነት መጠን ይለካል። SATን አብዛኛዎቹ ኮሌጆች እና ዩኒቨርሲቲዎች ለቅበላ እና የነፃ-ትምህርት (ስኮላርሽፕ) ዕድሎች ይጠቀሙበታል።

ሁሌም በስፕሪንግ፣ የኮሎራዶ የአሥራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች SATን እንዲሁም የCMAS ሳይንስ እና ሶሻል ስተዲስ ምዘናዎችን ይወስዳሉ። ከዚህ በታች ያለው ሠንጠረዥ የስቴት ፈተናዎችን በክፍል ደረጃ ያሳያል፡-

| | |
|---|---|
| ከ3ኛ - 8ኛ ክፍሎች | የኮሎራዶ የትምህርት ስኬት መለኪያዎች (CMAS) |
| 9ኛ ክፍል | PSAT 9 |
| 10ኛ ክፍል | PSAT 10 |
| 11ኛ ክፍል | SAT፣ CMAS ሳይንስ፣ CMAS ሶሻል ስተዲስ |

## ልጁ የሚፈተነው/የምትፈተነው መቼ ነው?

SAT በወረቀት እና እርሳስ ቅርጸትን በመጠቀም ኤፕሪል ውስጥ ይሰጣል። ፈተናው አማራጭ ከሆነ የ50-ደቂቃ የጽሑፍ (ኢሴይ) ክፍል ጋር በግምት 3 ሰዓት ይወስዳል። ስለ ዝርዝር የፈተና የጊዜ-ሰሌዳ መረጃ ለማግኘት የልጅዎን ት/ቤት ይጠይቁ።

አማራጭ የሆነው ኢሴይ አንዳንዶች የሚመርጡት ቢሆንም በሁሉም ኮሌጆች እና ዩኒቨርሲቲዎች ተፈላጊ መስፈርት አይደለም። ተማሪዎች እና ቤተሰቦች አማራጭ የኤሴይ ክፍሉ ምርጫቸው በሆኑ ዩኒቨርሲቲዎች ተፈላጊ መስፈርት መሆን/አለመሆኑን እንዲመረምሩ ይበረታታሉ። ተማሪዎች የኤሴይ ክፍሉን ቢወስዱ የሚከተሉት ጥቅሞች የሚያገኙ ይሆናሉ፡-

- ተማሪው ለኮሌጅ የሚያስገባቸውን ማመልከቻዎች ያጠናክርለታል።
- ተማሪው የመጻፍ ብቃቱን እንዲረዳ ያግዘዋል።

## ልጁ ምን ውጤት(ቶች) ይሰጠዋል/ታል?

ተማሪዎች በ400 እና 1600 መካከል የሆኑ ውጤቶችን ያገኛሉ። ይህ ውጤት ተማሪዎች በሒሳብ እና ንባብ እና ጽሕፈት ክፍሎች የሚኖራቸውን ዕድገት/ለውጥ ጥምር ውጤቶች ይወክላል። በSAT ላይ የተማሪ አፈጻጸም ደረጃ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማስረጃው (ትራንስክሪፕት) ላይ ይካተታል።

## እነዚህ ውጤቶች እንዴት ጥቅም ላይ ይውላሉ?

እነዚህ ውጤቶች በመላ ሀገሪቱ ውስጥ በብዙ ኮሌጆች እና ዩኒቨርሲቲዎች ለቅበላ ዓላማ እና የነፃ-ትምህርት ዕድሎችን (ስኮላርሽፖችን) ለመስጠት ያገለግላሉ።

## ተጨማሪ መረጃ

በልጅዎ ትምህርት ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ እናበረታታዎታለን። ልጅዎን በቤት ውስጥ ማገዝ ስለሚችሉባቸው መንገዶች እና ሊገኙ ስለሚችሉ የፈተና አገዛዎች (አቅርቦቶች) ለመጠየቅ ወደኋላ እንዳይሉ እባክዎ።

**ለተጨማሪ መረጃ፡- ደረጃዎች/ስታንዳርዶች እና ምዘናዎች**
የሚከተሉትን ድር ጣቢያዎች ይጎብኙ፡-

- http://assessments.dpsk12.org
- http://parents.collegeboard.org

**ግብዓቶች፡- PSAT እና SAT**

ለአዲስ SAT የየዕለት ልምምድ | ኮሌጅ ቦርድ

- በየዕለቱ የናሙና ጥያቄዎችን ያግኙ፤ ወዲያውኑም ግብረ-መልስ ያግኙ።
- ተማሪዎች በመደበኛነት እንዲለማመዱ ያስችላቸዋል።
- ተማሪዎች የታተሙ የመልስ መስጫ ወረቀቶችን ተጠቅመው የPSAT ወይም የSAT የልምምድ ፈተናዎችን መሥራት ይችላሉ። ከዚያም ፎቶ አንስተው "ስካን እና ስኮር" የሚለውን ማስፈጸሚያ /function/ መጠቀም ይችላሉ።

ኦፊሲያላዊ የSAT ልምምድ | Khan አካዳሚ

- ተማሪዎች ለመለያ (አካውንት) ይመዘገቡ እና በPSAT እና SAT ውጤቶቻቸው መሠረት ግለሰባዊ የሆኑ ሊያሻሽሉ የሚገባቸው መስኮች ላይ ምክር ወይም ጥቆማ ያገኛሉ።
- ሙሉ ርዝመት ያላቸው የልምምድ ፈተናዎች፣ የምርመራ ሙከራዎች /diagnostic quizzes/፣ የየዕለት የልምምድ ጥያቄዎች እና ለተወሰኑ የፈተናው ዘርፎች የታለሙ የመዘጋጃ ግብዓቶች በKhan አካዳሚ ድር ጣቢያ በነፃ ይገኛሉ፡- https://www.khanacademy.org/mission/sat.

PSAT ልምምድ | የወንዶችና ሴቶች ልጆች ክበብ

- ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን ተማሪዎች ከSAT እና PSAT የመስመር ላይ ግብዓቶች ጋር ለማገናኘት ከወንዶችና ሴቶች ልጆች ክበብ /oys & Girls Club/ ጋር አጋርነትን ፈጥረናል።

ስለምዘናዎቹ ጥያቄዎች ወይም ሀሳቦች ካሉዎ፣ የልጅዎን ት/ቤት በቀጥታ ያነጋግሩ ወይም የቤተሰብ የምርጫ ክልል /Constituency/ አገልግሎትን በ(720) 423-3054 ደውለው ያነጋግሩ።